Center for
Well-being of
Africans in
America

CWAA

P.O. Box 25339, Seattle, WA 98165-2239 Tel: 206-925-4800 www.cwaaUSA.org

*AMHARIC*

ሃምሌ(ጁላይ) 31, 2008

የተከበሩ ወላጅ፤

በአሜሪካ የሚገኙ አፍሪቃውያን ደህንነት ማእከልና(CWAA) የሲያትል ትምህርት ቤቶች የቤተሰብና የኮሚኒቲ ሽርክና ጽህፈት ቤት((OFCP) ለትምህርት ቤት የደረሱ ልጆች ያላቸውን ከምስራቅ አፍሪቃ አገሮች የመጡ ወላጆች በኮሚኒቲ በሚደረጉ ውይይቶች እንዲሳተፉ ጥሪ ያደርጋል። ወላጆች ስለልጆቻቸው ያላቸውን ልምድ ለመስማት ፍላጐት አለን። ይህ ውይይት በአነስተኛ ቡድኖች ከ 8 እስከ 10 ወላጆች በሚገኙበት "የትኩረት ቡድን" የሚል ስያሜ በተሰጠው አማካይነት የሚከናወን ነው።.

የዚህ የትኩረት ቡድን አላማ መረጃን ለመሰብሰብና ከምስራቅ አፍሪቃ የመጡና በአሜሪካ የሚገኙ ወላጆች ያካበቷቸውን ልምዶችና ፈታኝ ሁኔታዎች በይበልጥ ለመረዳት እንዲያስችለን ነው። ከዚህ መረጃ ደግሞ ወላጆች ልጆቻቸውን በሚያሳድጉበት ወቅት የሚያጋጥማቸው ፈታኝ ሁኔታዎች ለመቋቋም የሚያስችላቸውን ምክርና ዘይቤ ከባህላቸው ጋር የማይጋጭና ተገቢ የሆነ ፕሮግራም ለመንደፍ ያስችለናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን። ከእኛ ጋር የሚካፈሉት መረጃ በአሁኑ ወቅትና በፊታችን ላሉት ትውልዶች ወላጆችና ልጆቻቸው እጅግ ጠቃሚ መዋእል ነው። ይህ የትኩረት ቡድን ውይይቱን የሚያካሂደው ስልጠና በወሰዱና ቋንቋዎን በሚናገሩ ግለሰቦች ነው።

በዚህ ጥናት ለመሳተፍ ከወሰኑ እስከ 10 የሚሆኑ ወላጆች በሚገኙበት ቡድን ከአንድ ሰአት ተኩል እስከ ሁለት ሰአት የሚፈጅ ስብሰባን ያካሂዳሉ። የትኩረቱ ቡድን መሪዎች የወላጆችን ልምድ በሚመለከትና ነጻ ሆነው የሚፈልጉትን ያህል ሃሳብ ለመስጠት የሚያመቻቸውን ጥያቄዎች ይዘው ይቀርባሉ። በውይይቱ ወቅት የቀረቡትን አስተያየቶች ሙሉ በሙሉ ለመጻፍ እንድንችል ውይይቱን በቴፕ እንዲቀረጽ እናደርጋለን። ነገር ግን በውይይቱ ወቅት የተሳታፊዎችን የመጀመሪያ ስም ብቻ እንጠቀማለን። የተሳታፊዎቹ ሌላ ስም በመዝገብ አይቀመጥም። የተሰጡትን አስተያየቶች ከስሞች ጋር አናዛምዳቸውም። ይልቁንም የተሰጡትን አስተያየቶች ስም የሌለበት እንዲሆን እናደጋለን።

በአሜሪካ የሚገኙ አፍሪቃውያን ደህንነት ማእከልና (CWAA)የሲያትል ትምህርት ቤቶች የቤተሰብና የኮሚኒቲ ሽርክና ጽህፈት ቤት (OFCP) ከምስራቅ አፍሪቃ የመጡ ወላጆች መካከል በጐ የሆነ የአስተዳደግ ልምድን ለመገምገምና ለማበልጸግ ወስነዋል። ልምድዎን በሚያካፍሉበት ወቅት በሁሉም ዘንድ ተመሳሳይነት ያለውን መልእክት እንድንቀስምና ብሎም አላማ ያለው መፍትሄን ለመፈለግ ያስችለናል የሚል እምነት አለን። በትኩረት ቡድኑ መሳተፍዎን ለማመስገን አነስተኛ ገንዘብ እንሰጣለን።

በዚህ ለመካፈል ፈቃደኛ ከሆኑ እባክዎን ካሮሊንን በቴሌፎን ቁጥር 206-234-4837 ደውለው ያነጋግሩ። ወይም ሊንዳ ስሌተርን በቴሌፎን ቁጥር 206-252-0992 ደውለው ያነጋግሩ። የእርስዎ መሳተፍ እጅግ ጠቃሚያችን ነው። ስለዚህ አብረውን እንደሚሰሩ ተስፋ እናደርጋለን።

አክባሪዎ

*ካሮሊን ሳዌ*